ቁጥር OFAGF03.13/2/52
ቀን 5/07/2015

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለተከበሩ አቶ አህመድ ሽዴ
የገንዘብ ሚኒስትር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የገንዘብ ሚኒስቴርን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የገንዘብ ሚኒስቴርን የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 8 ገጽ ኦዲት ሪፖርት እና 19 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 27 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያዘን የላክን መሆኑን እንገለጻለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ጌታሁን ደምጤ
የፋይናንስና ኮምፕሊያንስ መስቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የገንዘብ ሚኒስቴር

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት /2015
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
ኦዲት ሪፖርት

የገንዘብ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የገንዘብ ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የገንዘብ ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር የ2014 የሂሣብ ሪፖርት ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በኢንስቲትዩት የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1. የሕክምና ቦርድ የሰጠው ማስረጃ ሳይኖር የተፈጸመ የውጭ አገር የሕክምና ወጪ

   ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፤ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላትና የህዝብ ተወካዮች መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 653/2009 መሰረት የሚገባቸውን ጥቅማ ጥቅም ውስጥ የሕክምና አገልግሎት በተመለከተ፤

   ሀ/ ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

   ለ/ የሕክምና ቦርድ በሚሰጠው ማስረጃ ውጭ አገር በመንግሥት ወጪ መታከም ይችላል ይላል፡፡

   ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ 5 የቀድሞ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ወደ ውጭ አገር ሄደው ለታከሙበት በድምሩ ብር 1,806,833.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ወደ ውጭ ሀገር ሄደው እንዲታከሙ የሕክምና ቦርድ የሰጠው ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2. በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ

   የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ሁለት የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጭዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩን እና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈጸም እንደማይገባ መመሪያው ይገልጻል፡፡ መ/ቤቱ ክፍያዎችን በወቅቱ እየፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ወጪዎች ናሙና ኦዲት ሲደረግ፦

   - ለውጭ ሃገር እና ለሀገር ውስጥ ለአውሮፕላን ትኬት ክፍያ ብር 265,723.00
   - የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሴቶች ቀን /ማርች 8 በዓል ለማክበር የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 84,700.00

በድምሩ ብር 350,423.00 ከበጀት ዓመት ዉጪ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ መፈፀሙ በኦዲት ተረጋግጧል

3. <u>ስራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል በ2014 በጀት ዓመት ለአገልግሎቱ ከተፈቀደው የመደበኛ በጀት ውስጥ በየፕሮግራሙ ከ10% (በመቶ) በላይ ያልተሰራበት በጀት መኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ከመደበኛ በጀት በድምር ብር 6,211,205.59 እና ከካፒታል ብር 6,388,286,786.37 በድምር ብር 6,394,497,991.96 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

1. <u>የአላቂና ቋሚ ንብረቶች አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ</u>

የፌዴራል መንግስት የንብረት አሰተዳደርና መመሪያ ቁጥር 9/2003 በክፍል አራት አንቀጽ-20 የመንግስት ንብረት ስለማስወገድ በንዑስ አንቀጽ-1 ከፊደል ሀ-መ በተገለጸው መልኩ የማይፈለጉ ንብረቶችን በንዑስ አንቀጽ-2 በተጠቀሰው የአወጋገድ ስርዓት መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች ማስወገድ እንደሚችሉ ተገልጸዋል፡፡

<u>በተመላሽ የንብረት ክፍል ውስጥ</u>

በቁጥር 58 የሚሆኑ ላፕቶፖች፣ 12 ዴል ኮምፒውተሮች ፣ 9 የሚሆኑ ዩፒኤስ፣ መለያ ቁጥር ያላቸው 8 የሚሆኑ ኤችፒ ኮምፒውተሮች ፣ መለያ ቁጥር የሌላቸው 16 የሚሆኑ ኤችፒ ኮምፒውተሮች ፣ በቁጥር 4 የሚሆኑ ቴሌቪዥኖች ፣ በቁጥር ወደ 55 የሚሆኑ አሮጌ የተሽከርካሪ ጎማዎች ፣ በቁጥር 5 የሚሆኑ ፕሮጀክተሮች ፣ በዓይነት ከ34 በላይ የሆኑ የተለያዩ ብዛት ያላቸው ቶነሮች ፣ ጌጋ ባይቱ ያልተገለጸ እና መለያ ቁጥር የሌላቸው በቁጥር 72 የሚሆኑ ፍላሽ ዲስኮች፣ 2,870 የሚሆኑ የሀትመት ቀለሞች ፣ በቁጥር 14 የሚሆኑ የእንግዳ ወንበሮች፣ የተለያዩ ዓይነት የፕሪንተር ቀለሞች እና 2 ዋሪት የውሃ ማጣራያዎች እና ሌሎችም ከተጠቃሚ ክፍል ተመላሽ የተደረጉ ሲሆኑ ነገር ግን መስራት አለመስራቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ በአሮጌ ተመላሽ ንብረት ክፍል ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፤

በቻናል አንድ እና ኢፍሚስ ንብረት ክፍል

በቁጥር 191 UPS ከ3 ዓመት በላይ በስቶር ቋሚ ንብረት ክፍል አገልግሎት ሳይሰጥ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም ለክልሎች መሰራጫት የነበረበት ከስድስት ዓመት በላይ ወጪ ሳይደረግ ለረጅም ጊዜ የቆየ በቁጥር 35 የሚሆን CISCO Router በንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት ሳይሰጥ የሚገኝ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ተመላሽ ያልተደረጉ የአሮጌ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን በተመለከተ

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ 9/2003 አንቀጽ 16 ቁጥር 2 በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲሸጡ ከተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ላይ ጠቃሚ አካሎችን ፈቶ አግባብ ባለው የእቃ አስተዳደር መሰረት ገቢ እንዲሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም በጨረታ እንዲሸጡ ማድረግ እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ተቋሙ በተገለጸው መሰረት ስለመስራቱ ሲረጋገጥ፡-

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተለያዩ ድርጅት ጋር ውል በመግባት የተቋሙን መኪናዎች ሲያስጠግን በድምሩ ብር 977,239.29 ለተለያዩ ድርጅቶች ክፍያ ሲፈጽም በአዲስ የተቀየረው እቃ አሮጌ የመለዋወጫ እቃ ወደ ተቋሙ ንብረት ክፍል ገቢ ለመደረጉ የአሮጌ እቃ ገቢ ደረሰኝ ከወጪ ሰነዱ ጋር ያልተያያዘ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2. **የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ**

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል። በዚህ መሰረት የሚኒስትሩ የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ ኦዲት ሲደረግ ሚኒስትሩ ካሉት ተሽከርካሪዎች ዉስጥ፡-

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት. 4-14236 ቶዮታ V8፣ የሞተር ቁጥር 1VD-0020651 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወደ ገንዘብ ሚንስቴር ያልዞረና በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ስም የተመዘገበ መሆኑ፣

➢ የሰሌዳ ቁጥር 4-00852 ኒሳን ፓትሮል ፣ የሞተር ቁጥር TD42132248 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወደ ገንዘብ ሚንስቴር ያልዞረና በኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ስም የተመዘገበ መሆኑ፣

➢ የሰሌዳ ቁጥር 4-08387 ቶዮታ ፕራዶ ፣ የሞተር ቁጥር 5L-5365994 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወደ ገንዘብ ሚንስቴር ያልዞረና በሲቪል ሰርቪስ ስም የተመዘገበ መሆኑ

➢ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት የማይሰጡ 9 ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

የህግ ደንብና መመሪያ ጉዳዮች (Compliance Issues)

1. ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ

በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፣የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ ብሎ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ 2002 መሰረት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 15/2 እና 15/3 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግዥዎችን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

ከተለያዩ ሆቴሎች የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 2,906,892.62 ያለውድድር በቀጥታ ግዥ በማከናወን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. <u>በጨረታ መገዛት ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ</u>

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 33 ቁጥር 4 በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ስርዓቶችን ለማሻሻል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት መፈጸም የሚገባቸውን የእቃ፤ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል የለባቸውም ይላል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ፍላጎትን አሰባስቦ ጨረታ ግዥ መፈጸም ሲገባው

- የተሽከርካሪ ጎማ ግዥ 8 ጊዜ ብር 707,448.00
- የተሽከርካሪ ማስዋቢያ እና መለዋወጫ ግዥ 11 ጊዜ ብር 721,503.00
- ጽህፈት መሳሪያ ግዥ 6 ጊዜ ብር 674,209.35
- የተለያዩ ጥገናዎች ግዥ 4 ጊዜ ብር 1,604,002.54
- የደንብ ልብስ ግዥ 3 ጊዜ ብር 724,071.65
- የአበባ ማስቀመጫና አካባቢ ማስዋብ ግዥ ብር 418,340.04

በድምሩ ብር 4,849,575.15 በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ በማከናወን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እያወራረደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ2014 በጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ላይ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 5217108 ብር 854,132.11
- በሂሳብ መደብ 5217110 ብር 77,272.15
- በሂሳብ መደብ 5217112 ብር 117,504.83
- በሂሳብ መደብ 5217205 ብር 269,036.74

• በሂሳብ መደብ 5217399 ብር 89,287.81

በድምሩ ብር 1,407,233.64 ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት ሳይሰበሰብ የቆየ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>ውዝፍ ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ</u>

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በሰኔ 30/2014 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ ብር 14,431.19 ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት